የሰ/መ/ቁ. 25048

ታህሣሥ 01/2000

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. ወ/ት ሒሩት መለሠ

4. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

5. አቶ ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ ግርማ ግዛው - ወኪል ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አስናቀች - ደምሴ ቀረቡ፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ የቀረበው የኑዛዜ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት እህታቸው እማሆይ ወርቁ ደምሴ ያደረጉላቸው ኑዛዜ እንዲፀድቅላቸው አመልክተዋል፡፡ ፍ/ቤቱ ኑዛዜው በተናዛዥና በአራት ምስክሮች ፊት መነበቡን የሚገልጽ ጽሁፍ በኑዛዜ ሠነዱ ላይ አልተካተተም በማለት ኑዛዜው ፈራሽ ነው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህንን ውሣኔ በመቃወም የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ኑዛዜው ሊፀድቅ የሚገባ ነው ብሎ ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁን አመልካች የሟች ልጅና ብቸኛ ወራሽ መሆኑን፣ ሟች የተውት ኑዛዜ አለመኖሩን ገልፆ ኑዛዜው እንዲፈርስላቸው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት መቃወሚያ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የሟች አለመሆኑን ክደው ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ፊርማው እንዲመረመር ትዕዛዝ የሠጠ ቢሆንም ፊርማው ቀለም ስላነሰው መለየት እንዳልተቻለ የፌዴራል ፖሊስ የፎረንሲክ ምርመራ መምሪያ ገልፆለታል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ኑዛዜው ሊፀና ይገባል? አይገባም? የሚለውን ጭብጥ ይዞ ኑዛዜ ላይ የነበረውን ምስክሮች ቃል ከሠማ በኋላ ምስክሮቹ ኑዛዜውን ሲያናገዙ የነበሩና የሠሙ መሆኑን ስላስረዱና ኑዛዜው ላይም ኑዛዜውን ሲናዘዙ

የነበርንና የሠማን ስለሆነ መስማማታችንን በተለመደው ፊርማችን እናረጋግጣለን በማለት ስለተገለፀ ኑዛዜው ሊፀና ይገባል በማለት የመጀመሪያውን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ቅሬታቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የአሁን የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎት ኑዛዜው በምስክሮች ፊት የተነበበ መሆኑ የተገለፀው ከምስክሮቹ ፊርማ በኋላ ሆኖ ሣለ ኑዛዜው ይፀድቃል መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ እንደተረዳነው ተጠሪ ሟች ያደረጉላቸው ኑዛዜ እንዲፀድቅላቸው ጠይቀዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት ኑዛዜው ግልጽ ኑዛዜ በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. መነበቡንና ይህም ፎርማሊቲ መፈፀሙን ስላልተመለከተ ፈራሽ ነው በማለት ወስኗል፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ኑዛዜው ሊፀድቅ ይገባል በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ የሻረው አንደኛ ኑዛዜው በምስክሮች ፊት ለመነበቡ በኑዛዜው ላይ ተገልጿል፡፡ ሁለተኛ ደግሞ ምስክሮቹ ቀርበው ኑዛዜው ሲደረግ የነበሩና የተነበበላቸው መሆኑን አስረድተዋለ በማለት ነው፡፡ ነገረ ግን እኛ የኑዛዜውን ሠነድ እንደተመለከትነው ምስክሮቹ ኑዛዜው ሲደረግ የነበሩና የሠሙ ስለመሆኑ የተገለፀው ከተናዛዢና ከምስክሮቹ ፊርማ ሥር ነው፡፡ በፍ/ሕ/ቁ. 890/1/ ሥር ደግሞ አንድ ግልጽ የሆነ ኑዛዜ በጽሁፍ ህዳግ ላይ ወይም በመስመሮቹ መካከል ወይም ከምስክሮች ፊርማ በኋላ ተጨማሪ ነገሮች ያሉበት ሲሆን ፊራሽ እንደሚሆኑ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም በተያዘው ጉዳይ በኑዛዜው ላይ ኑዛዜው በምስክሮች ፊት በመነበቡ የሚገልፀው ጽሁፍ ከምስክሮቹ ፊርማ በኋላ የተጨመረ መሆኑ በግልጽ እየታየ ኑዛዜው እንዲፀድቅ መደረጉ ከፍ ሲል የተመለከተውን ሕግ ያላገናዘበ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የኑዛዜ ሰነዱ ቀርቦ እያለ በኑዛዜው ላይ የተመለከቱትን ምስክሮች ሠምቶ ኑዛዜው እንዲፀድቅ መደረጉ በፍ/ሕ/ቁ. 2006/2/ን የሚቃረን ነው፡፡ ምንም እንኳን ይህ ድንጋጌ ቀጥተኛ ተፈፃሚነቱ ለውል ግንኙነቶች ቢሆንም ግዴታዎቹ ከውል የተገኙ ባይሆንም ስለ ውል በጠቅላላው የተደነገጉት ደንቦች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 1677/1/ ሥር ስለተመለከተ ይኸው የፍ/ሕጉ ቁጥር 2006/2/ም ለኑዛዜ ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም በኑዛዜው ላይ ስለተፃፈው ነገር የሰው ምስክሮችም ሆነ የሕሊና ግምት ማስረጃ ሊቀርብ ስለማይገባ ፍ/ቤቱ ምስክሮቹን ሠምቶ መወሠኑም ሕጋዊ አልነበረም፡፡

በአጠቃላይ የክርክር ምክንያት የሆነው ኑዛዜ እንዲፀድቅ መደረጉ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1/ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 04237 በ21/03/98 የሰጠው ውሣኔና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22938 በ05/07/1998 የሠጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡

2/ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 776/93 በ2/09/93 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

3/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ